## የእግዚአብሔር ቁጣና ዓመፀኞች

***ንባብ:-*** 1:18-32

***ዓላማ:-***

-የእግዚአብሔር ፅድቅ በወንጌል አማካይነት የተገለጠበትን ምክንያት ማመልከት ።

-ሰው ሁሉ በአንድ መንገድ ብቻ እንደሚፀድቅ ማረጋገጥ።

-ፅድቅ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ማረጋገጥ።

***መግቢያ:-***

በቀደመው ትምህርት እንዳየነው ወንጌል አንድ ብቻ ነዉ ።ይህም ወንጌል የእግዚአብሔር ፅድቅ የተገለጠበት ወንጌል ነዉ ። የእግዚአብሔር ፅድቅ የተገለጠበት ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንደሆነ እና ይህን ወንጌል በእምነት መቀበል አስከትሎት እንዳለው በቃሉ አይተናል ።በዛሬው ትምህርት ደግሞ **የእግዚአብሔር ቁጣና ዓመፀኞች ያላቸውን ግንኙነት ከእግዚአብሔር ፅድቅ መገጥ አንፃር እንመልከት ።**

### 1: *የእግዚአብሔር ፅድቅና የአመፀኞች የአሁን ሁኔታ*

1:1 ከሰማይ በተገለጠው የእግዚአብሔር ቁጣ ስር ናቸው።

1:2. ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮዎች ሆነዋል።

1:3 እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጥቶአቸዋል።

1:4 የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ ታልፈው ተሰጥተዋል።

### 2: *ዓመፀኞች ለምን በዚህ ሁኔታ ተገኙ?*

2:1 እውነትን በአመፅ ስለከለከሉ

2:2 እግዚአብሔርን በልኩ ስላላከበሩት።

2:3 እግዚአብሔርን በልኩ ስላላመሰገኑት።

2:4 የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ፍጡር ስለለወጡ።

2:5 እግዚአብሔርን ለማወቅ ስላልፈለጉ።

### 3: *የዓመፀኞች መጨረሻ ሞት ነዉ ።*

3:1 መንፈሳዊ ሞት

3:2 አካላዊ ሞት

3:3 የዘላለም እሳት ባህር ቅጣት።

***ማጠቃለያ:-***

መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምርው ኃጢአት ሁሉ ዓመፅ ነው ዓመፅም ሁሉ ኃጢአት ነው። እንዲሁም ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል ስለሚል ሁሉ አመፀኞች ናቸው። ስለዚህ ሁሉም ከእግዚአብሔር ቁጣ ስር የሚድኑበትም መንገድ የላቸውም ። ስለዚህ ከዚህ ቁጣ እንዲድኑ በወንጌል የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፅድቅ

ያስፈልጋቸዋል ።ይህንንም በልጁ ሲያምኑ ያገኙታልና በልጁ ሊያምኑ ይግባል ምክንያቱም በርሱ በሚያምን
አይፈረድበትምና።